


-በአበራ ለማ

አየሁት ደግ ልብህን፥
እያየ እማያየውን ውስጥህን፤
አየሁት ደግ ልብህን፥
ተትርፉ መስጠት ያልቻለውን፤
አየሁት ደግ ልብህን፥
የንፉግ ንፉግ እልቅናህን
…ደሞም ደሞም…
በጎ በጎ መርገጫህን፤

አየሁት ያን ውርስህን፥
ያያት አያት ቅሪትህን፤
የተራበ እንዳይበላ፥
የተጠማ እንዳይጠጣ
የታወከ እንዳያርፍ፥
የታሠረ እንዳይወጣ
ወጥመድ መረብ ማገጃህን፥
አየሁት ያን ውስጥህን፤

አየሁት ደግ ልብህን፥
ጨካኝ ጥርሶቹን ነክሶ
በክፋት ጭምብል ጨምብሶ፥
ባሉባልታ መንበር ነግሦ፤
አየሁህ ወዳጄ፥
እያለህ የለሁም ብለህ
እያየህ ላታየኝ፥
ከምቅ ጓዳ ተጨንቡለህ፤
ወገን ሞረሽ ሲልህ፥
ጆሮህን ተለጉመህ
አየሁህ ስታየኝ፥
ተመንገዴ ልታነቅፈኝ፤

አየሁት ደግ ልብህን፥
እውነትን ማየት ፈግሞ
አየሁት ቋንጂል መስሎ፥
ሳይወደኝ ወዶኝ ታሞ፤
አየሁት የውስጥ ውስጥህን፥

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ለቁርጥ ቀን ያኖርኩትን
ሳይኖር ኑሮ፣
ታልኖረበት ያሻሁትን፤

አየሁት ያን ልብህን፣
አጋም ተቀጋ አሽቶ
እንደር'ደ ምድር ሲንቀረቀብ፣
ቁልቋል ምስለ'ኔን ወግቶ፤
አየሁት አዞኛ ሲያለቅስ
ሱናሚኛ ሲርመሰመስ…
እግዚኦ ልብ ይማር!…
የልብ አምላክ የ'ጅ አይነፍግ
ታኅበር ቢሸሸጉ፣
ገልጦ መውጋቱን አይገድፍ…

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com